New Generation of Human Rights Defenders | 2022

CARD
የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY
MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF GAME!

# አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ!

## ለሰብዓዊ መብቶች የሚሟገት ትውልድ መገንባት!

Nurturing a Generation that Stands for Human Rights!




ታኅሣሥ 2015
December 2022

**CARD**

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF GAME!

## ስለ ካርድ

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ /ካርድ/) ቦርድ-መር፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 113/2011 መሠረት፣ በመዝገብ ቁጥር 4307፣ ሐምሌ 17፣ 2011 ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው።

ካርድ በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ማየት ራዕይ አድርጎ ሰንቆ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

## ለበለጠ መረጃ


**Email:** info@cardeth.org

**Website:** www.cardeth.org

**Phone:** +251 116-671 657

አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ



**Book Layout Design:** Armonium Solomon

# ማውጫ


አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ! 1

"ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት" 3

የዘንድሮ ሠልጣኞቻችን ምን ይላሉ ? 8

ስኬታማዎቹ የአምና ሠልጣኞች 16

የአሠልጣኞች ምልከታ 19

ስለመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) 24

# አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ!



በረዥም ዓመታት የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ሰብዓዊ መብቶችን የሚያከብር ዴሞክራሲያዊ ስርዓተ ማኅበር የመገንባቱ ሒደት እስካሁን አልተሳካም። በየጊዜው የሚከሰቱ የፖለቲካ ለውጦች ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ያላቸው ቁርጠኝነት እምብዛም ዘላቂ ሲሆኑ አይስተዋልም። ለሰብዓዊ መብቶች የሚታገሉ ተቋማት እና ግለሰቦች ቁጥርም ከሕዝብ ብዛታችን አንፃር ዝቅተኛ ነው። በዚህም ምክንያት ከተፈጥሯዊ የሰው ልጅ ነፃነት እና ክብር የሚቀዱትን ሰብዓዊ መብቶችን የኢትዮጵያ መንግሥት እንዲያከብር፣ እንዲያስከብር፣ እና ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ሁኔታዎችን እንዲያሟላ የሚያደርግ ሕዝባዊ/ትውልዳዊ መሠረት አልተጣለም ማለት ይቻላል።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፣ ምንም እንኳን ሰብዓዊ መብቶች ሕገ መንግሥታዊ ከለላ ቢሰጣቸውም፣ በተግባር ግን በመላው ኢትዮጵያ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት በርካታ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን ሲፈፅሙ ይታያል። ሕገ ወጥ ግድያዎች፣ ፆታዊ ጥቃቶች፣ የዘፈቀደ እስር፣ የማሰቃየት ተግባር፣ ወዘተ የተለመዱ ክስቶች ናቸው። ሐሳብን የመግለጽ እና መረጃ የማግኘት እንዲሁም የመሰብሰብ እና የመደራጀት መብቶችም አላግባብ በተለያዩ ማነቆዎች ስለሚገደቡ ዴሞክራሲያዊነትን መገንባት አልተቻለም። በተለይ የሰብዓዊ መብቶቹ ጥሰቶች ደግሞ ግጭቶች በየአካባቢው በተፋፋሙባቸው ሁኔታዎች ውስጥ እጥፍ ድርብ ይጨምራሉ። እነዚህ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ለዘለቄታው እንዲቀረፉ የበርካታ ባለድርሻ አካላት የተቀናጀ ርብርብ አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር በአዲሱ ትውልድ ዘንድ የሰረፀ የሰብዓዊ መብቶች አረዳድን መገንባት በወደፊቱ ዘመን ላይ አስተማማኝ መሠረት እንደመጣል ነው።

በኢትዮጵያ እስከ 70 በመቶ የሚደርሱት ሕዝቦች ዕድሜያቸው ከ35 ዓመት በታች ነው። እነዚህ የዚህ ትውልድ አባላት የሰብዓዊ መብቶችን እሴቶች አንግበው ከተነሱ፣ ኢትዮጵያ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሰብዓዊ መብቶች የሚከበርበት ስርዓተ ማኅበር ሊኖራት ይችላል። የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት 'አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ' የተሰኘ ፕሮጀክት በመቅረፅ ዓመታዊ እና ተከታታይ የሥልጠና ዕድሎችን ፍላጎቱ ላላቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች በመስጠት ላይ ይገኛል። ይህም በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ራዕዩን ለማሳካት ከሚያደርጋቸው የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ የማድረግ ተልዕኮው ውስጥ አንዱ ነው።

የአዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ ተከታታይ ሥልጠና በ2013 እና 2014 የትምህርት ዓመታት የተጀመረ ሲሆን፣ በመጀመሪያው ዙር ተከታታይ ሥልጠና 364 በአዲስ አበባ የሚገኙ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች እንዲያገኙ ማድረግ ተችሏል። ከመጀመሪያው ዙር ሠልጣኞቻችን መካከል በየትምህርት ቤቶቻቸው የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ማሳደጊያ ንቅናቄዎችን የጀመሩ አሉ። ሥልጠናውን በ2015ም በመቀጠል ተዳራሽነታችንን በማስፋት በአዲስ አበባ እና በክልል ከተሞች 370 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችን ማሠልጠን ችለናል። በሥልጠናው የተሳተፉ ተማሪዎች በቴሌግራም ቡድን በሚደረግ ውይይት ዘላቂ የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ማሳደጊያ እንዲያደርጉ የሚበረታቱ ሲሆን፣ በየትምህርት ቤታቸው ንቅናቄዎችን ሲመሠርቱ ማበረታታቻ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

የአዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ ተከታታይ ሥልጠና ላይ የታደሙ ተማሪዎች በየትምህርት ቤቶቻቸው የሰብዓዊ መብቶች ክለቦችን እንዲያቋቁሙ ጥረት እያደረግን ቢሆንም፣ በአገር ዐቀፍ ደረጃ በትምህርት የሰብዓዊ መብቶች ክለቦችን እንዲያቋቁሙ አልተፈቀደላቸውም። ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ቤቶች ውስጥ እንዲቋቋሙ የሚፈቅዳቸው የክለብ ዓይነቶች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች ክለቦች እንዲካተት ጥረት ማድረጋችንን እንቀጥላለን።

**በፍቃዱ ኀይሉ**
**የካርድ ዋና ዳይሬክተር**

**ዴሞክራሲን ብቸኛው የጨዋታ ሕግ ማድረግ!**

# "ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት"

## የኢሰመኮ ዋና ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ መልዕክት

የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን (ኢሰመኮ) **"ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት"** የሚለውን ራዕይ እንደ ተቋም የምናራምደው ብቻ ሳይሆን፣ መላው የኮሚሽኑ ባልደረቦች እንደ ኢትዮጵያዊያን፣ እንደ ነዋሪ፣ እንደ ባለድርሻ እና እንደ ሰው በጽኑ የምናምንበት እና እውን እንዲሆን የምንፈልገው ነው። ይህ ራዕያችን ሁለት ዋና ዋና ሁናቴዎችን ያካትታል።



የሰብዓዊ መብቶች ባሕል ማለት አንድም ባለመብቱ (right-holder) ያለ ስጋትና ፍርሃት፣ እንዲሁም ያለ አስታዋሽና ያለ ግርታ መብቱን የመጠየቅ እና የሚጠይቀውን መብት ግዴታ ፈጻሚ አካል (duty-bearer) የሚያውቅበት ሁኔታ መፈጠርን ያመላክታል። በሌላ በኩል ሰብዓዊ መብቶችን የመጠበቅ፣የማክበር፣ የማስከበር እና የማሟላት ግዴታ ያለባቸው አስፈጻሚ አካላት የሁሉንም ሰዎች እና ባለድርሻዎች መብቶች አውቀው፣ ተረድተው፣ አምነውበት የሚተገብሩበት

ብቻ ሳይሆን፣ መብቶቹ ሳይተገበሩ ቢቀሩ ተጠያቂነት እንደሚኖር የሚገነዘቡበትና በተግባር የሚረጋገጥበት አሠራር መዘርጋትን ያሳያል። የዚህ ዓይነት ባሕል ሲሰፍን የሰብዓዊ መብቶች መጠበቅ፣ መከበርና መሟላት እንደመደበኛ ሁኔታ፤ የሰብዓዊ መብቶች መጣስ ደግሞ እንደልዩ ሁኔታ የሚታይ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ወቅታዊም ሆነ ታሪካዊ ሁኔታ ይህንን ባሕል ለመፍጠር ገና ብዙ መንገድ እንደሚቀረን ያሳያል፤ በአንዳንድ ወቅትም ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባትን ሀገር ማየት እጅግ አዳጋች፣ በአጭር ጊዜ የማይፈጸም አልያም ጭራሹን የማይሆን ሊመስል ይችላል። ሆኖም ይህ አስተሳሰብ የሀገራችንን እና የሕዝቧን በርካታ ፈታኝ ጊዜያት የመቋቋም ብሎም ድል የማድረግ ታሪክ የሚዘነጋ፤ እንዲሁም በተለይም ሀገር ተረካቢ የሆነውን ወጣት እና ታዳጊ ትውልድ ብዛት፣ አቅም እና የቴክኖሎጂ እና ፈጠራ ግኝቶችን ተጠቅሞ የመሥራት ችሎታውን ከግምት ውስጥ ያላስገባ ነው።

በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው ከ18 ዓመት በታች መሆኑ እና በተለይም ከ14 እስከ 24 ዓመት ያለው ሕዝብ ቁጥር ከጎልማሳዎቹ እና ከአረጋውያን ቁጥር የላቀ መሆኑ በሕግ፣ በፖሊሲ፣ በተቋም ግንባታ፣ በሃብት ክፍፍል እና በአሠራር በአግባቡ ግንዛቤ ውስጥ ከተከተተ ለሀገሪቱ የሚያስገኘው ጥቅም ከፍተኛ ነው። የሀገራችን ታዳጊዎች እና ወጣቶች ቁጥር ከፍተኛ መሆን በሰብዓዊ መብቶች አተገባበር ላይም ተጽዕኖ የሚያሳድር ነው።

የመጀመሪያው ተጽዕኖ በክልሎችም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ የሚተገበሩ፣ ከሰብዓዊ መብቶች ጋር ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውና በመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚከናወኑ ተግባራት፣ የሚቀረጹ ሕጎችና ፖሊሲዎች ተጠቃሚዎች ወይም ተጎጂዎች በዋነኛነት እነሱ መሆናቸው ነው። በሴቶች መብቶች፣ በመፈናቀልና በፍልሰት ወይም በሰብዓዊ መብቶች ትምህርት ዙርያ የሚከናወኑ ተግባራት ስልታዊ በሆነ መልኩ ታዳጊዎችንና ወጣቶችን ታሳቢ ሳያደርጉም ቢሆን አብዛኛው ተጠቃሚዎች መሆናቸው አልያም የተጽዕኖው ተደራሽ መሆናቸው አይቀርም። ለምሳሌ ከንብረት መብት ወይም ከሠራተኛ መብቶች ጋር የተገናኙ እንደ የቤት መሥሪያ ብድር፣ አነስተኛ የደመወዝ ወለል ወይም የመሬት ፖሊሲ፣ አልያም አነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶችን የሚመለከቱ የግብር አሰባሰብ አሠራሮች በዋነኛነት የወጣቱን የሥራ ዕድል፣ ቤተሰብ የማፍራት ወይም በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ በመረጠው የሥራ ዘርፍ ተንቀሳቅሶ የመሥራት መብቱን ሊያመቻች ወይም ሊጎዳ የሚችል ይሆናል ማለት ነው።

በዛው ልክ በሰብዓዊ መብቶች ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና የሰብዓዊ

መብቶች ቀውስ ምክንያት የሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች፣ ጦርነት፣ ግጭቶችና ጥቃቶች ዋነኛ ተጎጂዎች ወይም ሰለባዎች ውስጥም በዚሁ የዕድሜ ክልል ያለው የማኅበረሰብ ክፍል ነው።

ይህ ነባራዊ ሁኔታ ከሀገሪቱ ሕዝብ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘውን የታዳጊዎች እና የወጣቶች ክፍል በሁሉም የሥራና ፖሊሲ ዘርፎች የማካተቱን አስፈላጊነትና ግዴታነት ከማስረዳቱም ባሻገር በእነዚህ ታዳጊዎችና ወጣቶች ላይ የሚጥለውን ኃላፊነት ወይም ከእነሱ የሚጠበቀውንም ሊያስገነዝብ የሚገባ ነው። በተለይም ወጣቶች በቁጥር ብዛታቸው ብቻ ሳይሆን ወቅቱና አካባቢያቸው የሰጧቸውን የአሠራር፣ የቴክኖሎጂ ወይም እሴቶችና አጋጣሚዎችን የማወቅና ጥቅም ላይ የማዋል፣ ስለአካባቢያቸው ሁኔታ መረዳትና መመርመር እንዲሁም እነዚህን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በባለቤትነት እና በይመለከተኛል መንፈስ ሊሳተፉና አስተዋጽዖ ሊያደርጉ ይጠበቅባቸዋል። የታዳጊዎችና ወጣቶች ተሳትፎ አስፈላጊነት ከታመነበት ወጣቶችና ሆነ ታዳጊዎች እራሳቸው ለመሳተፍ ተነሳሽነት ሊያሳዩና ሊሳተፉ፣ እንዲሁም ተሳትፏቸውን መጠየቃቸው የመብት ጥያቄም ብቻ ሳይሆን ኃላፊነትም ጭምር እንደሆነ ማስታወስ ያስፈልጋል።

የሰብዓዊ መብቶች ትምህርት መስፋፋት ታዳጊዎችና ወጣቶች ይህንን ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ በማስቻል ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ የሚያደርግ ነው። የሰብዓዊ መብቶችን ትምህርት እራሱ መብት የሆነበትና ትምህርቱንም ተደራሽ ማድረግ ግዴታ የሆነበት ምክንያት አንዱ ይሄው ነው።

ሆኖም ከትምህርት እና ከክህሎት ባሻገር ሰብዓዊ መብቶችን የመጠየቅ ልምድ ለማዳበርና በሰብዓዊ መብቶች ጉዳይ ላይ ለመሳተፍ በቅድሚያ በሰብዓዊነት ማመን እና የሰብዓዊነት ስሜት መጋራት ይገባል። ሰብዓዊነት ስለሁሉም ሰዎች እና ስለ ሁሉም ሕያው ፍጡሮች ያገባኛል፣ ይመለከተኛል፤ ኃላፊነት አለብኝ፣ እንዲሁም በሁሉም ሰዎች መካከል አንድነት እና ትስስር እንዳለ ማመን ማለት ነው። ስለዚህም ሰብዓዊነት በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት በሁላችን ደኅንነት ላይ የተቃጣ ጥቃትና ለሁላችንም ስጋት ሊሆን እንደሚችል ማስተዋልን ይጠይቃል። በእራስ ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ብቻም ሳይሆን በሌሎች ሰዎች ላይ የሚደርሰውን ጉዳትም ጭምር የመቃወም ጽናት የሚመነጨው ከዚህ እምነት ነው።

በሰብዓዊነት ለማመንና ሰብዓዊነትን ለመተግበር ደግሞ በቅድሚያ እራስን ማወቅ፣ እራስን መረዳትና በተለይም ደግሞ ለእራስ ክብር መስጠት ያስፈልጋል። ሁላችንም ከቤተሰባችንና ከአካባቢያችን ከምንወርሳቸው እሴቶችና ባሕሎች የሚውጣጣ

ማንነት ቢኖረንም ምን ዓይነት ሰዎች እንደምንሆን የመምረጥ ኃላፊነት ግን የግላችን ውሳኔ ነው።

ኃላፊነት መሸከም የሚችል ሰብዓዊነት የሚሰማው ሰው የመሆን ውሳኔ ግን ከእራስ የሚያጎድል ውሳኔ አይደለም፣ ይልቁንም ለእራስ የሚጨምር፣ የሚያጠነክርና የሚያሳድግ ነው። በሰብዓዊ መብቶች ሥራ ውስጥ የተሰማሩ ሰዎች ጥንካሬና ተስፋ ብሎም ወደተሻለ ጊዜ የመሄድ እርግጠኝነት የሚመነጨው ከዚህ እውነታ ነው።

የዛሬዋ የሀገራችን ታዳጊዎችና ወጣቶች ይህንን ሰብዓዊነት የመቀበልና የመኖር ውሳኔ ለመወሰን ተግዳሮት የሚሆንባቸው እንደ ሰላም እጦት፣ ሙስና፣ ድህነት፣ ፍልሰትና መፈናቀል የመሳሰሉ ፈታኝ ሁኔታዎች እንዳሉ ሁሉ በርካታ አስቻይ ሁኔታዎችንም ማስታወስ ያስፈልጋል።

የዛሬው ትውልድ በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሰብዓዊ መብቶችን መንገድና መርሆች በመከተል የእራሳቸውን ብሎም የሀገራቸውን ስም በበጎ ያስጠሩ ሰዎችን አርአያነት ለማጥናትና ለመከተል የሚያስችሉ መረጃዎችን በቀላሉ የሚያገኝበት፣ በአካባቢው ከሚታዘባቸው ችግሮች ጋር ለሚመሳሰሉ ችግሮች በሌሎች ሀገራት የተገኙ መፍትሔዎችን የሚመረምርበት እንዲሁም አዳዲስና ውጤታማ የሰብዓዊ መብቶች ሙግት ዘዴዎችን ጨምሮ የተለያዩ ተሞክሮዎችን የሚቀስምበት ዕድል አለው። በወቅታዊ ሁኔታ የሚታዩ አዳጋችና ፈታኝ ሁኔታዎችም ቢሆኑ ይህንን ሰብዓዊነት ለመተግበርና የመፍትሔ አማራጮችን ለማግኘት ዕድል የሚሰጡ ናቸው። የታዳጊዎቻችንና የወጣቶቻችንን ይህን የማድረግ አቅም በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ትምህርት ቤቶችንና የመጻሕፍት ቤቶችን በሚገነቡ፣ ለተጎዱ ሰዎች እርዳታ በሚያሰባስቡ እንዲሁም የትምህርት ዕድል ያላገኙ ልጆችን በሚያስተምሩ ወጣቶቻችን ላይ በየጊዜው የምንመለከተው ነው።

የእኔም ሆነ የኮሚሽናችንን **“ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት”** ራዕይም እንደሚሳካ ያለን እምነት በዋናነት በዚህ የሀገራችን ታዳጊዎችና ወጣቶች በብዛታቸው ለሀገራችን ባመጡት አዲስ ኃይል፣ በጊዜያቸው ባገኙት አዲስ ዕድልና በየቀኑ በሚያሳዩት አዲስ ፈጠራና አቅም ላይ የተመሰረተ ነው። ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሚሆኑት ታዳጊዎቻችንና ወጣቶቻችን ሰብዓዊነትን ለእራሳቸው ወስነው አቅማቸውንና ችሎታቸው ያስገኘላቸውን መፍትሔዎች ተጠቅመው ሰብዓዊነትን ለሌሎች ሲተገብሩ ነው። አዲሱ የሀገራችን ትውልድ የሰብዓዊነት መንገድ በጽኑ ፍላጎት እንዲመርጥ ፋና እና ምሳሌ የሚሆኑ ሰዎችንና መልካም ተሞክሮዎች ማሳየትና መምራት የእኔም ሆነ የባልደረቦቼ እንዲሁም

በሰብዓዊ መብቶች ሥራ ውስጥ የተሰማሩ ባለሞያዎች ሁሉ ከፍተኛ ጥረት ልናደርግበት የሚገባ ኃላፊነት ነው። ወጣቶችና ታዳጊዎችም **“ሰብዓዊ መብቶች ባሕል የሆኑባት ኢትዮጵያን ማየት”** የሚለው ራዕያችን የእናንተን የዛሬ አቅምና የነገ ሕይወታችሁን የሚያልም መሆኑን አውቃችሁ፤ ዛሬ በገጠመን ችግሮች ሳትሸነፉ ሰብዓዊ መብቶችን ባሕል የማድረግ የበኩላችሁን ኃላፊነት እንድትወጡ አደራ እላለሁ።

**ኮሚሽነር ዶ/ር ዳንኤል በቀለ፣**
**የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን!**



# የዘንድሮ ሠልጣኞቻችን ምን ይላሉ?



| ሥም፡ | የትምህርት ደረጃ፡ | ከተማ፡ | ዕድሜ፡ | ፆታ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ልደት ጥላሁን | 11ኛ | ድሬዳዋ | 18 | ሴት |

በመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የተሰጠው ሥልጠና የኔንም ሆነ ከኔ ጋር በሥልጠናው የተሳተፉ ተማሪዎችን አስተሳሰብ የሚቀይር ሥልጠና ነበር።

በመጀመሪያ ራሴን እንዳይ አድርጎኛል። በመቀጠል ድሮ የነበረኝ ዕውቀት ላይ የበለጠ ተጨምሮ ስለ ሰብዓዊ መብቶች፣ ስለ ስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ወዘተ ጥሩ ግንዛቤ እንዳገኝበት ረድቶኛል።

በካርድ የተሰጠው የሰብዓዊ መብቶች ሥልጠና በኔ ላይ የባሕርይ ለውጥ አምጥቷል ብዬም አምናለሁ። ስለ ፆታ እኩልነት እንዲሁም በትምህርት ቤት ውስጥ ሐሳብን በነፃነት መግለጽ በተማሪ ላይ የሚታይ ችግር አለ። ሥልጠናው እነዚህን ችግሮች እንዳጤንና ችግሮችን ለመወጣት መንገዶችን እንድቀይስ አድርጎኛል።

በዚህም ምክንያት፣ የሴቶችን ክበብ በማቋቋም የተማርኩትን ለማስተማር እንዲሁም እንደ አንድ ኃላፊነት እንዳለበት ዜጋ ከራሴ ጀምሬ በማኅበረሰቤ ዘንድ ጥሩ ግንዛቤ ለመፍጠር እንድንቀሳቀስ አድርጎኛል።



ሥልጠናው የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች እንድሆንና አነሳስቶኛል። በመጀመሪያ እንደ አሠልጣኞቼ ተማሪዎችን አሰልጥኜ እንዲያውቁ ማድረግ ፍላጎቴ ነው። ምክንያቱም የኔ መነሻ እነሱ ስለሆኑ ፈጣሪ ከፈቀደ ደግሞ የአገሬን ኅብረተሰብ የመቀየር ሕልም አለኝ።

በማኅበረሰቤ ውስጥ ለሴት ልጅ ያለው አመለካከትም እጅግ ዝቅተኛ ነው። በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉት እነዚህ አመለካከቶች ከግንዛቤ እጦት የመጡ እንደሆነ ከሥልጠናው በኋላ ተገንዝቤያለሁ። የተስተካከለ የስርዓተ ፆታ እኩልነት እንዳይኖር የግንዛቤ ማነስና እና ጎጂ የሆነ የባሕል ተፅዕኖ መኖሩ ገብቶኛል።

በሥልጠናው ወቅት የክርክር መነሻ የነበሩና የሳቅና የቀልድ መጀመሪያ የነበሩ ጉዳዮች ከሥልጠናው በኋላ ስንግባባቸው ተመልክቻለሁ። የክርክር ምክንያት የነበሩ የፆታ እኩልነትና የሰብዓዊ መብቶች ጉዳዮችም ዕውቀት ከተፈጠረባቸው በኋላ ለመደጋገፍ ስንበረታታም አስተውያለሁ።

ካርድ እነዚህን ሥልጠናዎች አስፋፍቶና ለሎችን ተማሪዎችም ማሠልጠን የሚችል እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ። እኔ የዚህ ሥልጠና አካል በመሆኔም እጅግ አመሰግናለሁ። ፈጣሪ ረድቷችሁ ተስፋፍታችሁና እንደ እኛ ሌሎቹን አስተምራችሁ አገራችንን እንደምትቀይሩ ባለሙሉ ተስፋ ነኝ።




| ሥም: | የትምህርት ደረጃ: | ከተማ: | ዕድሜ: | ፆታ: |
|---|---|---|---|---|
| ፌኔት ኬኔሳ | 10ኛ | ቢሾፍቱ | 15 | ሴት |

*እኔ ወደዚህ ሥልጠና ስመጣ ጠብቄ የነበረው በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ እውቀትና ሰፋ ያለ ዕይታ ማግኘትን ነበር። ከዚህ ባለፈም የተለያዩ ሰዎችን አመለካከት መረዳት፣ ከተለያዩ ትምህርት ቤት የመጡ ተማሪዎች ጋር ሐሳብ መለዋወጥ እንዲሁም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ኅብረት ማድረግን ጠብቄ መጥቻለሁ። በሥልጠናው እንዲሁም በሥልጠናው ወቅት ከሌሎች ተማሪዎች ጋር የነበረኝ ቅርርብ ይህንን ፍላጎቴን አሳክቶልኛል ብዬ አምናለሁ።*

*ሥልጠናው ካስጨበጠኝ እውቀት በተጨማሪም የሰዎችን ሐሳብና አመለካከት አመዛዝኖ ለመቀበል ያለኝን ክህሎት አዳብሪያለሁ።*

*ፆታ ላይ መሠረት ያደረጉ የተሳሳቱ አመለካከቶችን እንዴት መረዳት እንደሚኖርብኝና በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችን ግንዛቤ እንዴት መቀየር እንደምችልም ተረድቻለሁ።*






በዚህም ምክንያት፣ ሥልጠናው በለት ተለት ኑሯችን ውስጥ ከትንሽ ነገሮች ጀምሮ ግንዛቤ ለመፍጠር ከፍተኛ ፍላጎት ፈጥሮልኛል። ከዚህ ባለፈም፣ የተለያዩ የትምህርት ቤት ክንውኖች ውስጥ በመሳተፍ ክለቦችን ለማቋቋም አስባለሁ።

በእነዚህ ድርጊቶችም ማኅበረሰባችን ውስጥ የምናስተውላቸው የመብትና የፆታ እኩልነትን የተመለከቱ ጉድለቶችን ለመረዳት በመቻሌና የተዛቡ አመለካከቶችን ለማስተካከል የራሴን አስተዋፅኦ ለማድረግ ተነሳስቻለሁ። የተለያዩ ማኅበረሰቦች ለሴቶች የሰጡት ቦታ ሴቶችን ከወዶንች አሳንሶ የማየት ልማድን አስፋፍቷል። ምንም እንኳን አንዳንዴ እነዚህ አስተሳሰቦችን ምክንያታዊ ለማስመሰልና ለሴቶች መልካም በማሰብ የሚደረጉ እንደሆኑ አድርጎ የማቅረብ ፍላጎት ቢኖርም፣ ለፆታ እኩልነት ትንሽ የማይባል ክፍተት ፈጥሯል። ይህ ደግሞ ወንዶች ከሴቶች በተሻለ የተለይዩ ዕድሎች እንዲያገኙ አስችሏቸዋል።

ይሁንና፣ በስርዓተ ፆታ እኩልነት ላይ የተሰጠው ሥልጠና በጣም አስደስቶኛል፤ ምክንያቱም በራስ መተማመንን በይበልጥ እንዳዳብር አድርጎኛል። ከዚህ ባለፈም ሌሎች ሥልጠናዎችን በዘርፉ እንድወስድ እና የተማርኩትን እንድተገብር አበረታቶኛል።

ለዚህም ካርድን እጅግ አመሰግናለሁ። አሠልጣኞቼም ዕውቀት እና ልምድ ስላካፈላችሁኝ ከልብ የሆነ ምስጋና አለኝ።



| ሥም፡ | የትምህርት ደረጃ፡ | ከተማ፡ | ዕድሜ፡ | ፆታ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ናኦል ናስር | 11ኛ | ቢሾፍቱ | 16 | ወንድ |

በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የተሰጠውን የሰብዓዊ መብቶች ሥልጠና ከመውሰዴ በፊት ስለ ሰብዓዊ መብቶች፣ የስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለፅ እንዲሁም የመሰብሰብ መብቶች ላይ ያለኝ እውቀት ውሱን ነበር። በዚህም ምክንያት፣ በእነዚህ ዘርፎች ሥልጠና እንደሚሰጥ ሳውቅ ግንዛቤዬና ዕውቀቴ እንዲሰፋ አስቤ የተሳተፍኩ ሲሆን፣ ሥልጠናውን ከጠበቅኩት በላይ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

በሥልጠናውም ለአገራችን ጥሩ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች መሆን የሚይስችለኝንም እውቀት አግኝቼበታለሁ ብዬ አምናለሁ። ሥልጠናው በባሕሪዬ ላይ ለውጥ አምጥቷል ብዬም አምናለሁ።

ከዚህ ሥልጠና በኋላ በምማርበት ትምህርት ቤት በሚገኙ ክበባት ወስጥ በመሳተፍ ከሥልጠናው ያገኘሁትን ግንዛቤ ለተቀሩት ይህን ዕድል ላላገኙ ተማሪዎች ብሎም ጓደኞቼ ግንዛቤ ለማስጨበጥ አስባለሁ።

ሥልጠናው የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች እንድሆን በደንብ አነሳስቶኛል ባገኘሁት አጋጣሚ የማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ጨምሮ ሰብዓዊ መብቶች ለሰው ልጅ መሠረታዊ እንደሆኑ በማሳወቅ ለእነዚህ መብቶች መከበር ለመሟገት አስባለሁ።




ከዚህ ባለፈም፣ በማኅበረሰብና በባሕል አመለካከቶች ምክንያት ሴቶች ከወንዶች ያነሱ ተደርገው ሲታሰቡ ኖረዋል። እነዚህ አስተሳሰቦች ምን እንደሆኑ፣ እንዴት መለየት እንደምችልና እንዴት መለወጥ እንደምችል ተገንዝቤያለሁ። በተለይ "ሴት ልጅ አትችልም" የሚል ኋላ ቀር አስተሳሰብ በትውልዶች ውስጥ የቆየ አመለካከት በኛም ትውልድ እንደቀጠለና መልኩንም እየቀያየረ እንደሚገኝ ከዚህ ሥልጠና ለመረዳት ችያለሁ። በዚህም ዙሪያ ለውጥ ማምጣት በምችልባቸው ዘርፎች ለመሥራት ሥልጠናው ፍላጎትና ዝግጁነት ፈጥሮብኛል።

በአጠቃላይ ስለ ሰብዓዊ መብቶችና ስለ ስርዓተ ፆታ እኩልነት በዚህ ሥልጠና ያገኘሁት ትምህርት በልቤ ቀርቷል። በዚህም ምክንያት ካርድን ለማመስገን እወዳለሁ።




| ሥም፡ | የትምህርት ደረጃ፡ | ከተማ፡ | ዕድሜ፡ | ፆታ፡ |
|---|---|---|---|---|
| ሀዊ ደጀኔ | 11ኛ | አዲስ አበባ | 17 | ሴት |

በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የሰብዓዊ መብቶችን የተመለከተ ሥልጠና እንደሚሰጥ ከመምህራኖቼ ስሰማ፣ ይህ ሥልጠና ካሁን ቀደም በትምህርት ቤት ያልተማርኳቸውና የማላውቃቸዉን ከሰብዓዊ መብቶች ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ለማወቅ እና በቻልኩት አቅም ተግባራዊ ማድረግ እንድችል አልሜ ለመሳተፍ ያስችለኛል ብዬ ወሰድኩት። ሥልጠናውም እንዳሰብኩት ከመሠረታዊ የሰብዓዊ መብቶች ፅንሰ ሐሳቦች፣ የስርዓተ ፆታ እኩልነት፣ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ እንዲሁም የመሰብሰብ መብቶች ጋር በተያያዘ በቂ እውቀት አስጨብጦኛል።

ሥልጠናው ከዚህ በፊት በነበረኝ የሰብዓዊ መብቶች እውቅት ላይ ብዙ ነገር ጨምሮልኛል።

ከሴቶች መብቶች እና የስርዓተ ፆታ እኩልነት ጋር በተያያዘ በማኅረሰብ ውስጥ ብዙ ኋላ ቀር የሆኑና መስተካከል ያለባቸው አመለካከቶች እንዳሉ በዚህ ሥልጠና ለመረዳት ችያለሁ።

ልክ ይህንን ሥልጠና እንደሰጡን አሠልጣኞች እኔም በቻልኩት ልክ ስለጉዳዩ ብዙ እውቀት የሌላቸውን በአካባቢዬ ለሚገኙ እንዲሁም በትምህርት ቤት ላሉ ጓደኞቼ እውቀት ለማስጨበጥ አስቤያለሁ። በሥልጠናው ወቅት በነበሩ የልምድ ልውውጦች ምክንያት ሥልጠናው በውስጤ ቀርቷል ብዬ መናገር እችላለሁ። የሠለጠንባቸው ርዕሰ ጉዳዮች ከዚህ በፊት ማወቅ የምፈልጋቸው ስለነበሩም ውስጤ ሊቀሩ ችለዋል።

እኔ በዚህ ሥልጠና ላይ በመሳተፌ በጣም ዕድለኛ ነኝ። ይህንን አስተማሪ እና አሰደሳች ሥልጠና ስለሰጣችሁን ከልብ እናመሰግናለን። በዚሁ ቀጥሉበት።




| ሥም: | የትምህርት ደረጃ: | ከተማ: | ዕድሜ: | ፆታ: |
|---|---|---|---|---|
| ቃልኪዳን ተረፈ | 12ኛ | አዲስ አበባ | 18 | ሴት |



በመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) የሰብዓዊ መብቶች ሥልጠና እንደሚሰጥ ስሰማ ካሁን ቀደም በሥነ ዜጋና ሥነ ምግባር ትምህርት ስለማውቃቸው የሰብዓዊ መብቶች እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የጠለቀ ዕውቀት አገኝበታለሁ ብዬ አምኜ ነው ተሳታፊ የሆንኩት። ለሁለት ቀናት የተሰጠውም ሥልጠና የጠበኩትን ያገኘሁበት ሲሆን፣ ከአሠልጣኞቹ ያገኘሁት ልምድም በቂ ዕውቀት አስጨብጦኛል።

ሥልጠናውን ከወሰድኩ በኋላ ሰብዓዊ መብቶች ከሰው ልጆች ተፈጥሮ ነጣጥለን ልናያቸው የማንችል እጅግ መሠርታዊ መብቶች እንደሆኑ ተረድቻለሁ።

ከዚህ ባለፈም የፆታ እኩልነትን በተመለከተ በማኅበረሰብ ውስጥ ያለው የተዛባ አስተሳሰብ ተቀባይነት እንደሌለው ተገንዝቤያለሁ።

ከሥልጠናው ባገኘሁት ልምድና እውቀት ተጠቅሜ አካባቢዬ ላይ ብሎም ትምህርት ቤት ውስጥ ያሉ ጓደኞቼን ቀድሞ ከነበራቸው የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ላይ በቻልኩት አቅም ለመጨመር አስባለሁ።

ሥልጠናው ወደፊት የሰብዓዊ መብቶች መከበርን በተመለከተ ተሟጋች እንድሆን በደንብ አነሳስቶኛል ማለት እችላለሁ። ወደፊት የሥነ ልቦና ባለሙያ ሆኜም ይሄንን እውቀት ለሌሎች ሰዎች ማስተላለፍ እስቢያለሁ። ካርድም ይህንን የሥልጠና ዕድል ስለሰጠኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

# ስኬታማዎቹ የአምና ሠልጣኞች



የመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ) በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ የሚሰጠው ሥልጠና አንዱ ዓላማ ሥልጠናውን የወሰዱ ተማሪዎች በራሳቸው ከሚኖራቸው ዕውቀትና የባሕርይ ለውጥ በዘለለ ለሌሎች ዕውቀቶቻቸውን እንዲያካፍሉና በሰብዓዊ መብቶች ዙሪያ ያለው ግንዛቤ እንዲሰፋ ያለመ ነው፡፡ ከዚህ ጋር በሚጣጣም መልኩ፣ እ.ኤ.አ. በ2021 በአዲስ አበባ የሰብዓዊ መብቶች ሥልጠና ሲሰጥ የመጀመሪያ ተሳታፊ ከነበሩ ተማሪዎች መካከል በሥልጠናው ተነሳስተው በሚማሩበት ትምህርት ቤት ክበብ በመመሥረት ያገኙትን ዕውቀት ለሌሎች ተማሪዎች ያካፈሉት የአሚጎንያን ትምህርት ቤት ተማሪዎች ይገኙበታል፡፡

እነዚህ ተማሪዎች፣ በሥልጠናው ወቅት የተሰጣቸውን የሥልጠና ሞጁል በመጠቀም ተማሪዎችን በማሠልጠን የሰብዓዊ መብቶችን የሚያቀነቅን ክበብ ለማቋቋም በቅተዋል፡፡

የዚህ ክበብ መሥራች ከሆኑት መካከል ሶልያና ዶጁ ትገኝበታለች። ሶልያና በመጀመሪያ ዙር ሥልጠናውን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል የምትገኝ ስትሆን፣ በካርድ በተሰጣት ሥልጠና በመነሳሳት የመጀመሪያውን የሰብዓዊ መብቶች ክበብ ከጓደኞቿ ጋር በመሆን እንደመሠረተች ትናገራለች።






“በመጀመሪያ ካርድ በሰጠን ሥልጠና በመነሳሳት 14 አባላት ያሉት እና ተማሪዎችን ስለሰብዓዊ መብቶች የሚያሳውቅ የወጣቶች የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች የትምህርት ቤት ክበብ ለማቋቋም ወሰንን። ከዚያም በእኛ በተዘጋጀው የግምገማ ፈተና ውጤት መሠረት ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ 45 ተማሪዎችን መርጠን ከካርድ በተሰጠን ሞጁል ማሠልጠን ጀመርን፤” ትላለች ሶልያና። እርሷና ጓደኞቿ በክበቡ ውስጥ የነበራቸው ሚና የተመረጡትን ተማሪዎች ማሠልጠን ነበር።

ክበቡን ለማቋቋም በካርድ የተሰጠን ሥልጠና እጅግ አነሳሽ እና አነቃቂ ነበር የምትለን ደግሞ የክበቡ ሌላኛዋ መሥራች ሔቤሊና ተስፋአለም ስትሆን፣ ለትምህርት ቤታችን ኃላፊዎች ሐሳባችንን በመንገር ሰባት ልጆች ሆነው ጀምረው በኋላም በተጨመሩ ሰባት ልጆች ለ14 ክበብ ለመሥረት በቅተናል ትላለች።

እነርሱ በሚማሩበት ትምህርት ቤት ቅርንጫፍ ተማሪዎችን አስተባብረው ክበብ በመመሥረት ሥልጠናውን ያላገኙ ተማሪዎች እነርሱ ያወቁትን እንዲያውቁ

ከማድረግ ባለፈ፣ በሌሎች የትምህርት ቤቱ ቅርንጫፎች በመገኘት ንግግሮችን ያደርጉ ነበር። በተለያየ ጊዜ የተለያዩ አሠልጣኞችን በመጋበዝ ተማሪዎቹ በጊዜ አጠቃቀም እና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሥልጠና እንዲያገኙ ያስቻሉት ሶልያና፣ ሔቤሊና እና ጓደኞቻቸው፣ ለሠልጣኞቹም ለኛም ፍሬያማ የሆነ ጥሩ ጊዜ ነበረን ብለን አምናለን ይላሉ።

ሥልጠናውን ከወሰዱ በኋላ በተማሪዎቹ ላይ የራስ የመተማመን ዕድገትን፣ የንግግር ችሎታ መሻሻልንና ጥሩ የቡድን መናበብን እንደተስተዋለም ሶልያና አክላለች።

በክበቡ አማካይነት ሥልጠና የወሰዱ ተማሪዎች የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሲሆን፣ በዚህ የምስክር ወረቀት የመስጠት ዝግጅት ላይ የካርድን ዋና ሥራ አስኪያጅ ጨምሮ ጆት ሰልፍ ዲቨሎፕመንት ፕሮግራም ተወካዮች ታድመዋል።

እነ ሶልያና በወቅቱ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለነበሩ ከትምህርት ቤቱ ቢወጡም፣ ክበቡ መቀጠል ስላለበት ከሠልጣኞች ጋር ወይይት አድርገው በአዲሶቹ ሠልጣኞች መሪነት ክበቡ እንዲቀጥል አድርገዋል።

ሔቤሊናም “በ2014 የ12ኛ ክፍል ተማሪዎች ስለነበንና ትምህርት ቤቱን ለቀን የምንወጣበት ዓመት ስለነበር ከሁሉም ክፍል ተማሪዎችን በማሰባሰብ የብቃት ምዘና ፈተና አዘጋጅተን ብቃት እና ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች መርጠን የክለባችን አባላት ማድረግ ችለናል” በማለት፣ “ክለባችን የወጣቶች የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ክበብ ተብሎ ስለተሰየመ በሰብአዊ መብቶች ላይ በተመሠረቱ በርካታ ጉዳዮች ላይ ለመወያየት ተደጋጋሚ ስብሰባ እናደርግ ነበር” ስትል ንቅናቄያቸው ዘላቂነቱን ታወሳለች።

እንደ ሔቤሊና ገለጻ፣ ግባቸው ተማሪዎች መብቶቻቸውን በደንብ እንዲያውቁ እና ሐሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ፣ ብሎም በውስጣቸው ያለውን ነገር ለመናገር እንዳይፈሩ ለማስቻል የነበረ ሲሆን፣ ከአንድ ዓመት በኋላ በአባሎቻችን ላይ ውጤቱን ለማየት ችለናል ትላለች። እነዚህን ችሎታዎች ለሌሎች ተማሪዎች ከማስተላለፍ ባለፈም፣ እርሷ በሰዎች ፊት ለመናገር ትፈራና ትቸገር የነበር ቢሆንም፣ በዚህ ልምምድ “ከተደበቅኩበት መውጣት ችያለሁ” ትላለች።

ዋናው የክበቡ ዓላማም ተማሪዎች መብትና ግዴታዎቻቸውን እንዲያውቁ ማድረግ ስለነበር በትምህርት ቤት ሚኒ ሚዲያ ተጠቅመው ስለነዚህ ጉዳዮች መልዕክት ሲያስተላልፉም ተማሪዎቹ ይናገራሉ።

# የአሠልጣኞች ምልከታ

**አይተነው ደበበ፣** የሰብዓዊ መብቶች መሠረታውያን አሠልጣኝ




የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በሁለት መልኩ ሊታይ ይችላል። በአንድ በኩል የሰብዓዊ መብቶችን በሚመለከት ያለው የሕግ ማዕቀፍ እና ተቋማዊ አደረጃጀት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ በተግባር የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ምን ይመስላል የሚለው ነው።

የመጀመሪያውን ስንመለከት የ1987 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ 3 ለሰብዓዊ መብቶች ሰፊ ዕውቅና ይሰጣል። በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በአፍሪካ ኅብረት ማዕቀፍ ከተፈረሙ የተለያዩ ዓለም ዐቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሥምምነቶችም ኢትዮጵያ አብዛኛውን ፈርማ አፅድቃለች። ሕግ መንግሥቱም በአንቀጽ 13/2 ላይ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌዎች ሲተረጎሙ ከዓለም ዐቀፍ ሥምምነቶች ጋር በተጣጣመ መልኩ መሆን አለበት በሚል ደንግጓል። ከዚህ በተጨማሪ ሕገ መንግሥቱ ሦስቱም የመንግሥት አካላት (ሕግ አውጭው፣ ሕግ

አስፈጻሚው እና ሕግ ተርጓሚው) ሰብዓዊ መብቶችን የማክበር እና የማስከበር ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል። በመጨረሻም በሕገ መንግሥቱ የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን እና የሕዝብ ዕምባ ጠባቂ ተቋማት ነጻ እና ገለልተኛ ሆነው ሰብዓዊ መብቶች በአገሪቱ እንዲከበሩ የመደገፍ ሥራ እንዲሠሩ እውቅና ይሰጣል። በአጠቃላይ ከሕግ ማዕቀፍ እና ከተቋማት አደረጃጃት አንጻር ለሰብዓዊ መብቶች የተሰጠው ዕውቅና ጥሩ የሚባል ነው።

ሁለተኛውን፣ ማለትም ተግባራዊ አፈፃፀሙን በተመለከተ የኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች ሁኔታ በርካታ ችግሮች ያሉበት ነው። በሕገ መንግሥቱ እና በዓለም ዐቀፍ ሥምምነቶች ዕውቅና ያገኙት የተለያዩ ሰብዓዊ መብቶች በፖለቲካዊ ፍላጎት አለመኖር እና በሌሎች ምክንያቶች የተነሳ በተደጋጋሚ እና በተለያየ ቦታ ሲጣሱ ይታያል። በቅርቡ ያለውን ሁኔታ እንኳን ብንመለከት በአገሪቱ የተካሔደውን የፖለቲካ ለውጥ ተከትሎ የሰዎች በሕይወት የመኖር መብት፣ የአካላዊ ደኅንነት እና ነጻነት፣ የመንቀሳቀስ መብት እና ሌሎች ሰብዓዊ መብቶች በተለይ መንግሥታዊ ባልሆኑ የታጠቁ ኃይሎች እና በመንግሥት ኃይሎችም ጭምር እየተጣሱ ይገኛል። በሌላ በኩል የፖለቲካ ለውጡን ተከትሎ የታሰሩ እና የተከሰሱ ሰዎች መብቶች፣ የመደራጀት ነጻነት፣ ሐሳብን የመግለጽ ነጻነት፣ የዜጎች ፖለቲካዊ ተሳትፎ እና ሌሎች ዲሞክራሲያዊ መብቶች በአንጻራዊ መልኩ የተሻለ ጥበቃ እያገኙ ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው አንደኛው የሰብዓዊ መብቶች ተግዳሮት ስለሰብዓዊ መብቶች ያለው መረጃ እና እውቀት ውሱንነት እና የዴሞክራሲ ባሕል አለመኖር ነው። ከዚህ አንፃር በካርድ የሚሰጡት የአዲሰ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ (New Generation of Human Rights Defenders (NGHRDs)) ሥልጠናዎች ስለሰብዓዊ መብቶች ያለውን የመረጃ እና እውቀት ክፍተት ከመቀነስም ባሻገር ወጣቶች ዴሞክራሲን እንዲለማመዱ የሚያበረታታ እና የሚያነቃቃ ሥልጠና ስለሆነ ለሰብዓዊ መብቶች መከበር የራሱ የሆነ አስተዋጽዖ አለው። ከዚህ ባሻገር ሠልጣኞች በሥልጠናው ያገኙትን እውቀት እና ልምድ ወደ ማኅበረሳባቸው በማስፋት በተለይም ወደ ዩኒቨርሲቲ የሚገቡ ተማሪዎች ለሌሎች በማካፈል ለሰብዓዊ መብቶች መከበር ተሟጋች እንዲሆኑ ስለሚያግዛቸው በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በንግግር ለመፍታት እና ሰብዓዊ መብቶች እንዳይጣሱ ለማገዝ የመሪነት ድርሻ ይኖራቸዋል የሚል እምነት አለኝ።

ሥልጠናው በተሰጠባቸው አራት ጉዳዮች ላይ ሠልጣኞች መሠረታዊ እውቀት አግኝተዋል ብዬ አምናለሁ። ይህንንም በሥልጠናው ወቅት በሚደረጉ የቡድን

ውይይቶች እና ጥያቄ እና መልስ ወቅት፣ እንዲሁም በመጀመሪያ ዙር ሥልጠና ማጠናቀቂያ እና የምርቃት ፌስቲቫል ላይ በነበረ የጥያቄ እና መልስ ውድድር ላይ ለማስተዋል ችያለሁ። ከዚህም ባሻገር ወደ ትምህርት ቤታቸው ከተመለሱ በኋላ አንዳንድ ሠልጣኞች ያገኙትን እውቀት ለሌሎች በማስተላለፍ የሚያኮራ ሥራ ሠርተዋል። ለአብነት ከአዲስ አበባ አሚጎኒያን ትምህርት ቤት የመጡ ሠልጣኞች 60 የሚሆኑ ሌሎች የትምህርት ቤቱ ተማሪዎችን ለሁለት ወራት አሠልጥነው ለማስመረቅ ባዘጋጁት ፌስቲቫል ላይ እንድገኝ ተጋብዤ ነበር። በጊዜው በሌላ ሥራ ምክንያት ከከተማ ውጭ በመሆኔ ለመታደም ባልችልም ከሌሎች ተሳታፊዎች ባገኘሁት መረጃ የተሳካ ፕሮግራም እንደነበር ተረድቻለሁ። ከዚህ ባሻገር ግን የሥልጠናው ትኩረት በአራት ጉዳዮች ላይ ብቻ የተወሰነ እና ለሁለት ቀናት ብቻ የተሰጠ ከመሆኑ አንፃር ሥልጠናው ስለሁሉም ሰብዓዊ መብቶች ዝርዝር እውቀት እና ግንዛቤ አስጨብጧል ለማለት አይቻልም።

በመጀመሪያ የሰብዓዊ መብቶች መከበር ከግለሰቦች ነጻነት ባሻገር ለአገር እና ለማኅበረሰብ ዘላቂ ልማት፣ ዘላቂ ሰላም እና ፍትሕ መረጋገጥ ቅድመ ሁኔታ በመሆኑ ፖሊሲ አውጭዎች የሰብዓዊ መብቶችን መከበር እኩል ትኩረት መስጠት አለባቸው። በሌላ በኩል በመንግሥት አካላትም ሆነ በሌሎች መንግሥታዊ ባልሆኑ አካላት የሚፈጸሙ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች ከግንዛቤ እጥረት ጭምር ስለሆነ የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ ማስጨባጫ ሥልጠናዎች በመንግሥት ተቋማት እና እንደ ካርድ ባሉ ሌሎች ተቋማት እንዲካሔዱ የፖሊሲ አውጭዎች በበጀት እና በሕግ መደገፍ አለባቸው።

ሠልጣኞችም በዚህ ሥልጠና ያገኙትን ግንዛቤ በሌሎች ተጨማሪ ሥልጠናዎች እና በንባብ በማዳበር እንደሥማቸው አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ትውልድ በመሆን በኢትዮጵያ የሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩ የዴሞክራሲ ባሕል እንዲያድግ የመሪነት ድርሻ መወጣት አለባቸው።

ይህንን ሥልጠና ያዘጋጀው ካርድም ሠልጣኞች ያገኙትን እውቀት በሚገባ እንዲጠቀሙ እና የሥልጠናው ዓላማ እንዲሳካ ሠልጣኞችን ማገዝ እና መከታተል እንዲሁም ከሌሎች ተቋማት (ከሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን፣ ከሚመለከታቸው የመንግሥት ተቋማት፣ ከሚዲያ እና ከዩኒቨርሲቲዎች) ጋር ማገናኘት እና ማስተዋወቅ ይኖርበታል። ከዚህ በተጨማሪ ሥልጠናው ባልተዳረሰባቸው አካባቢዎች ያሉ ተማሪዎችም ሥልጠናውን እንዲያገኙ ሌሎች ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ የጀመረውን የሰብዓዊ መብቶች ግንዛቤ የማሳደግ ሥራ ሊገፋበት ይገባል።

## **አበባዬ አሥራት፣** የስርዓተ ፆታ እኩልነት አሠልጣኝ






ስርዓተ ፆታን ያህል አስፈላጊ በሆነ ርዕሰ ጉዳይ ከወጣት ለውጥ ፈጣሪዎች ጋር መሳተፍ አስደሳች ነበር። ስርዓተ ፆታ ለልቤ የቀረበ ርዕሰ ጉዳይ ነው እና ከመላው ኢትዮጵያ የተውጣጡ ወጣቶች ስርዓተ ፆታ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ላይ ስላለው ተፅዕኖ እና ለሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች የአካታችነት አስፈላጊነትን ለማስተማር ዕድሉን በማግኘቴ በጣም ተደስቻለሁ። ሠልጣኞቹ ወጣት፣ ንቁ እና የተሰጣቸውን አዲስ መረጃ ለማወቅ የሚጓጉ ነበሩ። ይህ እጅግ ከፍተኛ ዋጋ የምሰጠውና የአገራችንን የወደፊት ብሩህ ተስፋ ጭላንጭል እንድመለከት ያደረገኝ ነው።

ተማሪዎቹ ብሩህ እና በጣም ጥሩ የማመዛዘን ችሎታዎች ነበራቸው። ስለሰለጠኑባቸው ርዕሰ ጉዳዮችም ጥሩ ግንዛቤ ነበራቸው። የወንዶችን የበላይነት የሚያቀነቅን ስርዓት ለማንም የማይጠቅም እና በሁሉም የሚደገፍ ስርዓት አለመሆኑ ገብቷቸዋል። ተማሪዎች እና የካርድ ሠራተኞች የግል ልምዳቸውን ለሌሎች በማካፈል የሌሎችን አጠቃላይ ግንዛቤና አረዳድ ማሳደግ እና ማሻሻል ችለዋል።

በሥልጠናው መካከል የተነገሩና በልቤ ከቀሩ ታሪኮች መካከል እጅግ አስደማሚ የሆነውን አንድ ታሪክ ላጋራችሁ። አንድ ተማሪ እናቱ ፖሊስ መሆኗን ተናግሮ፣ እርሷ ተጠርጣሪዎችን ተከታትላ ስትይዝ ሰዎች ተጠርጣሪዎችን እርሷ ያዘች ብለው ሳይሆን የተሳካላት ተጠርጣሪዎቹ ስለተባበሯት ነው ብለው እንደሚያምኑ ተናግሯል። ይህ የሆነበትም ምክንያት አንዲት ሴት ብቁ ፖሊስ ልትሆን ትችላለች ብለው ስለማያምኑ ነው። ተማሪዎችም፣ ሴት ጠንካራ ናት ስንል ለችግሩ መባባስ አስተዋፅዖ በሚያደርግ መልኩ ጥቅም ላይ እንዳይውል ከፍተኛ ጥንቃቄ መደረግ እንዳለበትም አሳስበዋል። ተማሪዎች ሴት ጠንካራ ናት በሚለው አገላለፅ ስጋት እንዳላቸውም ገልጸዋል። አገላለፁ የሴቶችን ጉዳት ለማመካኘት ወይም ተጨማሪ ጉዳትን ለመጨመር ሰበብ መሆን የለበትምና በከፍተኛ ጥንቃቄ ጥቅም ላይ መዋል አለበት።

የኢትዮጵያ ማኅበረሰብ በአጠቃላይ ፆታን መሠረት ያደረጉ ጥቃቶችን ሰበብ በማድረግ ሴቶችን ተጠያቂ ያደርጋል። ተማሪዎቹም የማኅበረሰቡ ውጤቶች በመሆናቸው ከዚህ የተለየ አስተሳሰብ አልነበራቸውም። ምንም እንኳን በእያንዳንዱ ቡድን ውስጥ የተቃውሞ ድምፆች ቢኖሩም፣ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በመፈቃቀድ፣ በፆታ ተኮር ጥቃት እና በወሲባዊ ጥቃት ላይ ተጨማሪ ሥልጠናዎች ያስፈልጓቸዋል።

ለስርዓተ ፆታ መሟገት/ማቀንቀን የማያቋርጥ የቀደመ ዕውቀትን የመተው እና አዳዲስ ዕውቀትን መሸመት ይጠይቃል። ተማሪዎቹ ዕድገታቸውን እና ተሟጋችነታቸውን ለማጎልበት ምቹ በሆነ የዕድሜ ደረጃ ላይ ይህንን ሥልጠና ወስደዋል። በአጠቃላይ መርሐ ግብሩ ስኬታማ ነበር ማለት እችላለሁ። ምክንያቱም ተማሪዎች እንዲሳተፉ እና የሚፈልጉትን ለውጥ በኅብረተሰባቸው ውስጥ እንዲሠሩ ያደርጋል። እነዚህ የአዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ ወጣቶች እንዴት የሰብዓዊ መብቶች ጥበቃ እና ከለላ እንዲደረግላቸው እንደሚሟገቱ ለማየት ጓጉቻለሁ።

# ስለመብቶችና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ካርድ)

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ /ካርድ/) ቦርድ-መር፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 113/2011 መሠረት፣ በመዝገብ ቁጥር 4307፣ ሐምሌ 17፣ 2011 ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው። ካርድ በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ማየት ራዕይ አድርጎ ሰንቆ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

## ራዕይ፣

**በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ማየት።**

## ተልዕኮ፣

የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ።

## የካርድ አንኳር ዓላማዎች

- በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ባሕል እንዲያብብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን መሥራት
- የሰብዓዊ መብቶች እና የዴሞክራሲ ዕድገት ደረጃን በመከታተል እና በመገምገም መንግሥታዊ የሆኑ እና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ተጠያቂነት እንዲያዳብሩ ማድረግ

- የዴሞክራሲ ግንባታን ለማገዝ የሚያስችሉ ተፅዕኖዎችን ለማድረግ የምርምር ሥራዎችን መሥራት፣ የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት፣ እና የማግባባት ሥራዎችን መሥራት
- ለዴሞክራሲ ተቋማት ቴክኒካዊ እና ሙያዊ ድጋፍ መስጠት
- ሰብዓዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበራቸውን ለማረጋገጥ የፖሊስ ማቆያዎችን፣ የማረሚያ ቤቶችን አያያዝ እና የፍርድ ቤቶችን ሒደት መከታተል እና መገምገም
- ምርጫዎችን መታዘብ፣ የዜግነት እና የመራጮች ትምህርት መስጠት











CARD
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY








NAOL

CARD

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY

MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF GAME!

## ስለ ካርድ

የመብቶች እና ዴሞክራሲ ዕድገት ማዕከል (ሴንተር ፎር አድቫንስመንት ኦፍ ራይትስ ኤንድ ዴሞክራሲ /ካርድ/) ቦርድ-መር፣ ለትርፍ ያልተቋቋመ፣ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ 113/2011 መሠረት፣ በመዝገብ ቁጥር 4307፣ ሐምሌ 17፣ 2011 ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅት ነው።

ካርድ በሰብዓዊ መብቶች እሴቶች ላይ የቆመ ዴሞክራሲያዊ ባሕል ያበበባት ኢትዮጵያን ማየት ራዕይ አድርጎ ሰንቆ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች እና የዜጎች ማኅበራት ለሰብዓዊ መብቶች መከበር በመሟገት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር እንዲያሰፍኑ የሚያስችላቸውን የአቅም ግንባታ ማድረግ ተልዕኮ በማንገብ እየሠራ የሚገኝ ድርጅት ነው።

## ለበለጠ መረጃ


**Email:** info@cardeth.org
**Website:** www.cardeth.org
**Phone:** +251 116-671 657

አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ



**Book Layout Design:** Armonium Solomon

New Generation of Human Rights Defenders | 2022

CARD
የመብቶች እና ዲሞክራሲ ዕድገት ማዕከል
CENTER FOR ADVANCEMENT OF RIGHTS AND DEMOCRACY
MAKE DEMOCRACY THE ONLY RULE OF GAME!

# አዲስ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋቾች ትውልድ!

## ለሰብዓዊ መብቶች የሚሟገት ትውልድ መገንባት!

## Nurturing a Generation that Stands for Human Rights!




ታኅሣሥ 2015
December 2022